# ተባብሮ መዳን ወይስ ተበታትኖ ማለቅ?

አብዛኛው ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጲያዊ የሚስማማበት ጉዳይ ቢኖር የችግሮቻችን መጠን ፣ አይነቶችና ምንጮቻቸው ቢለያይም ቅሉ ፤ ችግሩ ግን በዘር ፣ በቀለም ፣ በጎሳ ፣ በጾታ ፣ በእድሜ ወዘተ ሳይለይ የያንዳንዱን ቤት በየተራ ማንኳኳቱ ነው። ኑሮ የከበደው ፤ ነጻነቱን ተገፎና ተረግጦ ያለው ፤ የተራበው ፤ ፍትህ የተጠማው እከሌ ተከሌ ሳይባል አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እንደሆነ ይታወቃል። ይሄ እውነት ከሆነ ታዲያ ለውጥ ማምጣት እንዴት ከበደን? የምር የተገፋና የመረረው ህዝብ እንዴት ዝም ይላል?

ምክንያቱ ደግመን ድጋግመን የሰማነው ፤ ነገር ግን በደንብ አላምጠን ውጠን ከዚያም ደግሞ መተግበር የተሳነን ጉዳይ ነው - **ተባብሮ በአንድነት መታገል አለመቻል!** ሰፊው ህዝብ በአንድነት መታገል ካልቻለ ደግሞ በተናጠል ጉዞ የአንዳችንንም ችግር መፍታት እንደማንችል በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በ97 ምርጫ ጊዜም በተግባር ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው። ወይ ተባብሮ መዳን ነው ፤ ካልሆነ ተሰባብሮ ማለቅ ነው *(We stand together or perish alone!)*

በመሰረቱ በህብረት መታገል እንደቃሉ ቀላል አይደለም። እንቅፋቶቹ አያሌ እንደሆኑ እሙን ነው። የበለጠ ከባድ ያደረገብን ግን ገዢው ቡድን በየጊዜው በሚያስቀምጥልን የመከፋፈያ ወጥመድ ውስጥ ሰተት ብለን መግባታችን ፤ ተያይዘም ግለሰቦችን በቡድን መፈረጅና መጨፍለቅ ልምድ ማድረጋችን ይመስለኛል። በከፋፍለህ ግዛ መርህ የረቀቁት ገዢዎቻችን በአንድ ላይ መቆም እንደማንችል እርግጠኛ ከመሆናቸው የተነሳ የስልጣን እድሜያቸውን በራሳቸው የህይወት ዘመን ብቻ ሳይሆን በምእተ አመት መትረው ያን ያክል ሊገዙን እንደሚችሉና እንደሚፈልጉ እየነገሩን ነው። እኛም ለዚህ ተመቻችተን እርስ በራሳችን ስንቆራቆስ እንገኛለን። የሰውን ልጅ በአስተሳሰቡና በስብእናው ከመመዘን ይልቅ መርጦ ባላመጣቸውና ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ቢፈልግም መቀየር በማይችላቸው ማንነቶቹና መገለጫዎቹ መሸፈን ለምደናል። ይሄ ኢዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ነው የሚለው እንዳለ ሆኖ እኔ ደግሞ ከዛም ባሻገር በአንድ ላይ ተደጋግፈን መቆም እንዳንችል እንቅፋት እየሆነብን ያለ ትልቅ ችግር ነው ብዬ አምናለሁ። ትግሉ የነጻነት፤ የፍትህ እና ሃገር የማዳን መሆኑ ይዘነጋና አንዲት ጋት ፈቀቅ ወደ ማያደርገን አተካሮ ውስጥ እየከተተን ነው።

የዘር አጥር አጥረን ልብ ለልብ መነጋገርና መግባባት እንዳንችል ጠላቶቻችን ሌት ተቀን እንደሚተጉ ይታወቃል። በተለይም ኦሮሞው ከአማራው እንዲናቆርና ፤ የተቀረው ኢትዮጵያዊ ከትግራይ ወገኑ ጋር እንዲናከስ ያልተፈነቀለ ድንጋይ የለም። የኢትዮጵያ ህዝብ ለነጻነቱና ለእናት ሀገሩ በህብረት የሚነሳበት እለት የአገዛዙ ፍጻሜ እንደሚሆን እነሱም ጠንቅቀው ያውቁታል። ለዚህም ነው የስልጣን እድሜያቸውን በልዩነቶቻችን ስፋትና መጠን ፤ እንዲሁም አንዳችን በሌላችን ላይ በምናሳድረው የጥላቻ ክረት የሚለኩት። አንድላይ መቆም ባለመቻላችን በራሱ በጅምላ ሳይሆን በየተራ ግን በርግጠኛነት ሁላችንም እንድንቀጠቀጥ እያደረገን ነው። እንደ አስፈላጊነቱም የሃይማኖትንም ልዩነት ለእድሜ ማራዘሚያነት እየተጠቀሙበት እንደሆነ በጅማና ደሴ ከተሞች የነበሩትን የቅርብ ጊዜ ዘግናኝ ክስተቶችን ማስታወስ በቂ ነው። ምናልባትም ወደፊት ይቺን ካርድ በሰፊው ይጫወቱባት ይሆናል።

በዘውጌና በሃይማኖት ልዩነቶች መባላታችን ለማናችንም እንደማይበጅ ደጋግመን የሰማነው ጉዳይ በመሆኑ ከዚህ በላይ ማሰልቸት አልፈልግም። በርግጥ ብዙዎቻችን ከመስማትና ከመበሳጨት ውጪ በደንብ አጣጥመን ስንኖርበት አይታይምና መደጋገሙ ምክንያታዊ ሊሆን ይችላል። ይቺን አጭር ጽሁፍ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ግን አልፎ አልፎ የሚነሱ ፤ አንዳንዴም ከህልቆ መሳፍርት ልዩነቶቻችን መካከል ለመቦደንና ለማግለል ሲባል ጎልተው የሚወጡ፤ በተለይ ውስጥ ውስጡንና ሰሞኑን ደግሞ በገሃድም በተቃዋሚው ጎራ የሚነሱና ሁልጊዜ ግራ የሚያጋቡኝ ሁለት ጉዳዮች ናቸው - የእድሜና የቦታ ልዩነቶች።

## ***ችግራችን የእድሜ አይደለም***

በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ የእድሜ ልዩነት እንደትልቅ ምክንያት ሆኖ ወጣቶች ስልጣን ካልጨበጡ ፤ ሽማግሌዎች አርፈው ካልተቀመጡ ፤ ያ ትውልድ ከፖለቲካው ድራሹ ካልጠፋ ወዘተ የሚል አይነት ክርክርና አስተያየቶች ከአንዳንድ አካባቢዎች እየሰማን ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚሰነዘረው አንዱ ፍረጃ በማሪክሲዝም አይዲዎሎጂ ያለፉ በሙሉ ከአመራሩ ይራቁ የሚል ነው። አንዳንድ ሰዎች የቀድሞ አስተሳሰብና አይዲዎሎጂ የማይለቅ በሽታ ነው ወይ ያሉትን ወደጎን ብንል እንኳን ይሄኛውም ግለሰቦችን በቡድን ጨፍልቆ የማሰብ ችግር ነው። መስራት የሚችለውንም የማይችለውንም ፤ ብሩህ አይምሮ ያለውንና የሌለውንም ፤ የተለወጠውንም ያልተለወጠውንም በጅምላ መፈረጅ ችግር አለው።

በርግጥ በየትኛውም ሀገር ወጣቶች የትግል አንቀሳቃሽ ሞተር መሆናቸው ይታወቃል። በራሳችንም ታሪክ እንዳየነው የተሳካም ያልተሳካም የለውጥ አብዮት ጀማሪዎችና አቀጣጣዮች ወጣቶች ናቸው። እኛ ወጣቶች ጉልበቱም፤ ወኔውም፤ ድፍረቱም ፤ አዲስ አመለካከቱም አለን። በተጨባጭ ያለወጣቶች ተሳትፎ ትግል ማሰብ የማይቻል ነው - በአመራሩም ጭምር። እንደ ብርቱካን ሚደቅሳ አይነት ለሃቅ የሚሞቱና ጀግና ወጣቶች በብዛት እንደሚያስፈልጉን አያከራክርም።

ነገር ግን ካለንበት አዘቅት ለመውጣት የሚደረገውን ትግል ወጣቶች ብቻ ካልመሩት ብሎ ማሰብ ስህተት ነው ብዬ አምናለሁ። ምንም እንኳን የቀደመው ትውልድ ያለፈበት ሂደት ከባድና መጥፎ ቢሆንም ፤ ከዛ ተሞክሮና የህይወት ልምድ ዛሬም ነገም ለሃገራቸው አንድነትና ለህዝባቸው ነጻነት የሚታገሉ ጀግኖች ሞልተዋል ብቻ ሳይሆን አሁንም የትግሉ አቀጣጣዮች ሆነው ብዙ መስዋእትነት እየከፈሉ ያሉ መሪዎች አሉን። በሳልና ለመጪው ትውልድ ቁምነገር ሰርተው ማለፍ የሚፈልጉ እጅግ ብዙ አዋቂዎች አሉ።

በአንጻሩ ደግሞ ውስጡ ያረጀ ወጣትና ፤ ውስጡም ውጭውም ያረጀ አዛውንት ሞልቶናል። በእድሜዬ ለሃገሬ ምን አደረግኩኝ ብሎ የማይጠይቅ ፤ ለነገዋ ጥሩ ወይም መጥፎ ሀገራችን ሃላፊነት አለብኝ ብሎ የማያስብ ፤ ስለሃገሩ ወቅታዊ ሁኔታ የማይከታተልና የማይቆረቆር ፤ በገዢው ቡድን የ18 አመት ያላሰለሰ የዘረኝነት ፕሮፓጋንዳ ውዥንብር ውስጥ ገብቶ የሚደናበር እዚህም እዛም ያለ ዜጋ ሞልቷል ፤ ነገር ግን ይሄንን በእድሜ መስመር በጭራሽ መለየትና መቦደን አይቻልም። ገና ብቅ ከማለቱ ያለብቃቱ ስልጣኑን ካልተቆጣጠርኩና ሰርቼ ሳይሆን ዘርፌ በልቼ ካልሞትኩ የሚል አስተሳሰብ ያለው ወጣት እንዳለ ሁሉ ፤ በቀረችኝ ጥቂት እድሜ አቅም ባይኖረኝም ስልጣን ይዤ ፣ ህዝብ ፊት ቀርቤ ፣ ታሪክ ሰርቼ ፣ ስሜን ተክዬ ምናም ልሙት የሚል የእንጨት ሽበት አይነት ሞልቷል። ታሪክ መስራቱ ባልከፋ ግን ያለ ችሎታና ያለስራ ሲሆን ትውልድ የመግደል ታሪክ ሆኖ ያልፋል። ስልጣን ኮርቻ ላይ ለመፈናጠጥ መሮጥና በትውልድ የሚታወስ ስም መትከል የሚቻለው ስልጣን ላይ ብቻ ነው ብሎ ማሰብ በራሱ የውስጥ ባዶነትን ያመላክታል።

ችግሩ የእድሜ እንዳልሆነ (ማብራራት ሳያስፈልገው)ብርቱካንና ልደቱን ማየት በቂ ይመስለኛል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ህዝብና የፓርቲ አባላትም ጥሩውን ከመጥፎ መምረጥና መለየት ይችላሉ ብሎ ማሰብ ጥሩ ነው - ብርቱካንን ከያቀብ፤ ያቆብን ከልደቱ ፤ ብርሃኑን ከያቆብ ፤ ግዛቸውን ከሃይሉ ወዘተ በእድሜ ሳይሆን በብቃት ሚዛን መዝነን መምረጥ እንችላለን። ግርማ ወ/ጊዮርጊስም ከልደቱ ሊመረጡ ይችላሉ። ቢያንስ እሳቸው ስራ አይሰሩም እንጂ ተንኮል አይሰሩም ሊባል ይችላል። ቁምነገሩ በፍጹም እድሜው ላይ አይደለም። ችግሩ ያለው ሰዎችን በብቃትና በስራ ብቻ መመዘን ልምድ ማድረግ አለመቻላችን ነው። መነጽራችን ብቃትና ስራ ከሆነ እድሜ ተጭኖት መስራት ያቃተውም ፤ ያረጀ የርዕዮተ ዓለም ጋኔል የተጠናወተና አለቅ ያለውም ፤ በወጣትነቱ የሚያጭበረብረውም ሳይወድ በግድ ይንገዋለላል።

ወጣቶች አመራሩን መረከብ እንዳለባቸው አበክረው የሚያሳስቡት አንዳንድ የአንድነት ፓርቲ ሰዎች በርግጥ ድርጅታቸው ውስጥ ያለውን ያፈጠጠ ችግር መሰረት አድርገው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የአመራር አባላቱ ላይ በግልጽ የሚታይ የብቃት ችግር አለ ብለን መስማማት ይቻል ይሆናል እንጂ ያ ችግር (በተለይ ደግሞ ሁሉም ላይ)ከእድሜና ካለፉበት አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ነው ብሎ መደምደም ቢያንስ አጨቃጫቂ ነው። በአንጻሩ ብዙዎቹ ወጣቶች ናቸው ተብለው ዝም አንልም የሚሉት የፓርቲው አባላት የሚሄዱበት መንገድ ራሱ ወጣቶቹ አመራሩን በሙሉ ይረከቡ የሚለውን አመለካከት ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል።

አመራር ላይ ለሚቀመጡ ሰዎች በርግጥ የእድሜ ለከት እንደሚያያስፈልግ አያጠራጥርም። "ይሄን ህዝብ አንቀጥቅጬ መግዛት ቢያቅተኝ ተንቀጥቅጬ እገዛዋለሁ" አሉ እንደተባሉት ፕሬዝደንታችን በየሄዱበት በሰውም በምርኩዝም በበርጩማም እየተደገፉ ስልጣን ላይ የሙጥኝ ሊባል አይችልም። ለምሳሌ የጡረታ ጊዜው የደረሰ ሰው አመራር ላይ መቀመጥ እንደማይችል መስማማት ይቻላል። ከዛ ውጪ ግን በየትኛውስ መስፈርት ነው አንድን ሰው ከአመራር ለማግለል ወጣት አይደለም ጎልማሳ አይደለም ምናምን የምንለው? ዞሮ ዞሮ ከእንደዚህ አይነት የቡድን ፍረጃ መላቀቅ በግድ ያስፈልጋል። ትግሉ ብቃት ባላቸው ሰዎች ይመራና ብቃትና ችሎታ ብቻ መሰረት ያድርግ እንጂ በወጣት ይሞላ በጎልማሳ ወይስ በሽማግሌ እያሉ መንቦጫረቅ የስቃያችንን እድሜ ከማራዘም ውጪ ምንም አይፈይድም።

### *ዳያስፖራውን መለየት*

ከሀገሩ ውጪ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ልክ እንደ ሌላ ሀገር ዜጋ ስለ ሃገሩ ምንም የማያውቅ ፤ እንዲሁም ምን አገባህ አይነት ደፋር አስተያየቶች ዘወትር በገዢው ቡድን አልፎ አልፎ ደግሞ ከተቃዋሚውም ጎራ ይደመጣል። በነገራችን ላይ ውጪ ያለውን ብቻ ሳይሆን ጭንቅ ሲይዛቸው ሀገር ቤት ያለውንም ህዝብ የከተማና የገርጠር ብለው ይከፍሉትና ፤ በገጠሩ ድጋፍ አለን የከተማው ምን ያውቅና ምንስ ያመጣና ይሉታል።

በቅርቡ ኢንጂነር ሀይሉ ሻወል ለፈጸሙት (በኔ እምነት) ትልቅ የፓለቲካ ስህተት ህዝብ ቁጣውን ሲያሰማባቸው ፡ "ዳያስፖራው ገንዘቡን ይዞ ገደል ይግባ እኛ እዚህ ከህዝቡ ጋር አብረን እየታገልን ነው" ነበር ያሉት። ሲጀምር ቁጣውን የገለጸው ሃገር ውስጥም ያለውም ህዝብ ነው። ሲቀጥል ደግሞ በገንዘቡም ፣ በጊዜውም ፣ በእውቀቱም ከጀርባቸው የነበረ ውጪ የሚገኘው ማህበረሰብ ዛሬ "ከባህሩ የወጣ አሳ" ሲሆኑ ተቃውሞውን ስላሰማ ምንም አታውቅም ማለት አለማወቅ ነው። በአጭሩ ይቺ ከገዢዎቻችን የተማሩት የመከፋፈል ስልት ነበረች። መፈረጅና መከፋፈልን አምባገነኖች እንዴት እንደሚጠቀሙበት ለማሳየት ያክል አነሳሁት እንጂ ዳያስፖራው በሚገባ ያዳመጣቸውና ትምህርቱን የወሰደ ይመስለኛል።

እንደኔ እምነት ሀገር ቤት ያለው ህዝብ በአሁኑ ወቅት የገፈቱ ቀማሽ ነው - በየእለቱ እየተራበ ፣ እየታሰረ ፣ እየተገደለ ያለው እዚሁ ያለው ህዝብ ነው። ነገር ግን ይሄንን ሃቅ ውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ አይከታተልም አያውቅም ማለት ፤ መከፋፈል ለሚሞክሩት ከንቱ ብልጠት

ለተቀበልናቸው ደግሞ ሞኝነት ነው። እኔ ስለሚደርስብኝ ችግር አውስትራሊያ ያለው አጎቴ አያውቅም ማለት ድካም ነው። እንዲያውም ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ አካባቢ ያለ ሰው ሌላው አካባቢ ስለሚፈጸመው ግፍና በደል ብዙ መረጃ አይኖረውም ማለት ድፍረት አይሆንም። ምክንያቱም በጭነቀት ውስጥ ያሉ አንዳንድ የግል ጋዜጦች ከሚያቀብሉት መረጃ ውጪ እንዳያወራ ታፍኖ ፣ እንዳይሰማና እንዳያይ ተጀቡኖ ያለ ህዝብ ነው። በተሻለ ውጪ ያለው ማህበረሰብ አጠቃላይ መረጃ አለው ብቻ ሳይሆን በትክክል እያስተጋባ ያለው አገር ቤት ያለውን ህዝብ ብሶት ነው ማለት መስማት ለፈለገ ሰው የማያጠራጥር ሃቅ ነው።

ትልቁና መረሳት የሌለበት ጉዳይ ግን ቁጥሩ እጅግ በጣም ብዙ የሆነው በስደት የሚኖረው ኢትዮጵያዊ እኮ በሀገሩ ውስጥ የሚደርስበት ጭቆና ፣ ግፍና የኢኮኖሚ በደል አንገፍግፎት የወጣ ነው። አንዳንዱም የመኖርና የመሞት ምርጫ ውስጥ ስለከተቱት ከሚወዳት ሀገሩና ቤተሰቦቹ የደም እንባ እያነባ እርቆ የሚኖር ዜጋ ነው። እንግዲህ እነዚህን በቀጥታ የግፍ በትር የቀመሱ ሰዎችንም ጭምር ጨፍልቀን ነው ስለሃገርህና ወገንህ ሁኔታ ምንም አታውቅም አርፈህ ተቀመጥ የምንለው። አንድ ለትምህርት ወጥቶ እንደማይመለስ ያጫወተኝ ወዳጄ ፤ ባእድ ሀገር እንዴት ትኖራለህ? ብዬ ስጠይቀው ፤ "ያው ሀገሬም እኮ ለኔ አሁን የባእድ ሀገር ሆናለች" ነበር ያለኝ። በዛ ደረጃ ሽንፈቱን ባልቀበለውም ፤ ልብ የሚሰብር ግፍ ፥ ቁጭትና ፥ ሀዘን እንደገፋው አያጠራጥርም።

በሌላ በኩል ሁሉም ከአንድ ቧንቧ የሚቀዳ ውሃ ይመስል ተማሪውንም ፥ ፓለቲከኛውንም ፣ ትናንት የወጣውንም ፥ 30 አመት የቆየውንም ፣ ተራማጁንም ፥ ጎታቹንም ፣ በየእለቱ ስለሃገሩ ጉዳይ ተቆርቁሮ ሲቆፍርና ሲያነብ የሚወለውንም ፥ ደንታቢሱንም ፤ አፈር ልሶ በሚያገኛት ሳንቲም ራሱን የሚስተውንም ፥ ወገኑና ሃገሩን ለመጥቀም የሚደክመውንም ወዘት አንድ ላይ ዳያስፓራ ብለን ጨፍልቀን ምንም አታውቅም ማለትና በአንድ ሚዛን መመዘን ከባድ ችግር ነው። ሰዎችን በቡድን ጨፍልቆ ማሰብ ይብቃን የምንለውም ለዚህ ነው። ለዲሞክራሲና ለሃገር አንድነት የሚጨነቅ ቀና መንግስት ቢኖረንና ውጪ ያለውን ማህበረሰብ የሚያሳትፍ ስርአት ቢፈጠርማ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ እርምጃዎች ወደፊት መራመድ እንደምንችል ብዙ አያከራክርም። በሌላ በኩል ውጪ ያለው ማህበረሰብ በአንድነት ተባብሮ መቆም ቢችል ፤ ወገኑን ከረሃብና ከባርነት እናት ሃገሩን ከመበታተን መታደግ የሚችል እጅግ በጣም ግዙፍ  አቅም እንዳለው ወዳጅም ጠላትም ያውቀዋል።

### *ማጠቃለያ*

እነዚህና ሌሎችም ማለቂያ የሌላቸው ልዩነቶቻችን ሁልጊዜ ሊያወያዩን ቢችሉም ችግራችን ግን በፍጹም ልዩነቶቹ አይደሉምና የዚህ አይነት አተካሮዎች ሊከፋፍሉንና ትኩረታችንን ከኳሷ እንድናነሳ እንዳያደርጉን መጠንቀቅ አለብን እላለሁ። የችግሩ ቀማሽ ሁሉም ነው ካልን ፤ በገዛ ሀገሩ እንደሁለተኛ ዜጋ የሚኖረው፤ የሚሰደደውና የሚታሰረዉ ፤ ነጻነትን የሚሻው ሁሉም ነው ካልን፤ ትግሉ ሀገር የማዳን እንዲሁም የመኖርና ያለመኖር ነው ካልን - ወጣት፣ ጎልማሳ ፣ ሽማግሌ ፣ አሮጊት ፣ ዳያስፖራ ፣ የከተማ ፣ የገጠር ፣ የሀገር ውስጥ ሳንል ሁሉም በቻለው መጠንና መንገድ መታገል አለበት። የመቦደን አካሄድ እናስወግድ !

***በያለንበት ለመለያየት ሳይሆን ለመተባበር እንስራ። የተባበረ ህዝብ ያለጥርጥር ያሸንፋል !***

ሳሙኤል ይሄነው

sami.yihenew@gmail.com